**ሕዝቡ እንዲያውቀው፣**




# <u>መጋረጃው ሲገለጥ፣</u>

ከትቂት ሳምንታት  በፊት "ሕዝብ እንዲያውቀው" በሚል እርዕስ አቶ ልደቱ (ክደቱ)፣ በለንደን ከተማ በወያኔ ኤምባሲ እርዳታ ስብሰባ ለማድረግ የነበራቸውን እቅድ ለሕዝብ አስታውቀን ነበር።

ሁኔታው እንደተደረሰበት፣ በድህረ ገጽ ላይ ይፋ በመሆኑ የተበሳጩት የወያኔ ኤምባሲ ባለስልጣኖች ስብሰባውን ለመሰረዝ የተገደዱ ሲሆን፣ በተያዘለት ቀጠሮ ክረምቱን አድፍጦ ከከረመበት አትላንታ ከተማ ወደ ለንደን ያቀናው የአስቆሮቱ ይሁዳ አቶ ልደቱ በኦግስት 31 ቀን 2009 ዓ.ም በማእከላዊ ለንደን ቻሪንክሮስ በሚባል አካባቢ፣ የቢራ መሸጭያ ቤት ውስጥ ዘጠኝ ያህል ሰዎችን በድብቅ ለማናገር ተገዷል። እንደ ዝርዝር ዘገባው ይሁዳው፣ ሁለት ነገሮችን አጠንክሮ የገለጽ ሲሆን፣

<u>አንደኛ፣</u> ቅንጅት ምርጫ 97ን እንዳላሸንፈና መንግስት ለመሆን የሚያስችለው አብላጫ ወንበር ፈጽሞ እንዳልነበረው፣

<u>ሁለተኛ፣</u> በግሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ተሳስቷል ብሎ እንደሚያምን እና "በግል ጋዜጦች እና በአክራሪ ጽንፈኞች እንደ ከብት በመነዳቱ የፖለቲካው ትግል ቅርቃር ውስጥ ከመግባቱ አልፎ ፖለቲካው እራሱ በአሥርተ አመታት ወደኋላ እንደተመለሰ ለዚህም ሕዝቡ እራሱን ተጠያቂ አድርጎ እና ከጭፍን ጥላቻ ተመልሶ በምክንያት መቃወምን ለመማር መንገዱን ቢጀመር ገና እንዳልመሸበት" ለመግለጽ ሞክሯል።

ሕዝብ የጣለበትን ሀላፊነት መሸከም አቅቶት ለዘረኞች እና ለነፍሰ ገዳዮች ያደረው እራሱ ነው። የክህደቱን ቁልቁለት ወርዶ…ወርዶ ያልጨረሰው ልደቱ፣ ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ህይወት እንድሌለው ጠንቅቆ ያውቃል። ክዚህ ሁሉ በደል በኋላ ሰማኒያ ሚሊዮን የሚሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ስለማያውቅ ነው ብሎ እርሱን ብቻ አዋቂ እና ለሕዝቡ የተላከ ብቸኛ መሲህ፣ ሕዝቡን ደግሞ ለድኅነት የተላከለትን አዋጅ ነጋሪ ከመቀበል ይልቅ ቀጥቅጦ በእንጨት ላይ ለመስቀል የሚፈልግ፣ ማስተዋሉ የተወሰደበት ሕዝብ አድርጎ መቁጠር፣ ቀጣሪዎቹን ለማስደሰት ከአልሆነ  በቀር ሌላ ምን ትርፍ አለው?
ቅንጅት ምርጫውን አላሸናፈም ሲል ድምጼ ይከበር በማለቱ በጠራራ ፀሀይ በአጋዚ ጥይት የተገደለው እና እደወጣ የቀረውን ንጹህ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ እንደ አቶ ልደቱ ስሌት ዓላማው በምርጫ ያጣውን ስልጣን በመፈንቅለ መንግስት ለማግኘት የሞከረ የወንበዴዎች የአመጽ እሩጫ ነበር ማለቱ ነው። ይህንን እማ ባለጊዜዎቹ የህወሀት ባለስልጣኖች ከአዲስ አበባ፣ የትግራይ ወጣቶች ከመቀሌ፣ ብለው…ብለው የጨሱት በመሆኑ አዲስ ነገር የለበትም፣ ዋናው ነገር ሕዝቡን ድምጽን ለማን እንደሰጠ ማወቁ ነው።

በአቆሮቱ ይሁዳ ሥር ለተገኛችሁ ጥቂት ሰዎች፣ የሕዝብ አይን ቀልቡን የነሳው አንድ ባንዳ ጋር በየስርቻው እንደ አይጥ በመሽሎክሎክ ትንሽም ቁም ነገር መስራት ይቻላል ብላችሁ ታስባላችሁ ይሆን?

ሌላው ቢቀር እንቢ ለነጻነቴ ብሎ በታላቅ ብሄራዊ ስሜት ገንፍሎ የወጣው የሚያዚያ 30ው ቀን የሕዝብ ማእበል ለቀረው አለም ሳይቀር ያስተላለፈው መልእክት፣ አባቶቹ የነጻነት ፋና ወጊ እንደነበሩ ሁሉ፣ አሁንም በዚህ ትውልድ የዲሞክራሲ ሥርአት እንደገና ከዚችው ከአፍሪካ ቀንድ እምብርት እንደሚወለድ ጭምር ነበር። አንድ ጽጌሬዳ አበባ ሳይቀነጠስ ለሰላም እና ለይቅርታ ያለውን ክብር አሳይቷል። በአለም ዙሪይ የተበተነው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን በጋራ ደግፎ የቆመው ለዚሁ ነበር። ይህንን እውነት መካድ እናንተም እነደኔ እበዱ ማለት ነው። ሁሉም ሲያብድ ደግሞ አስታማሚ ይቸግርና በሽታውም ይከፋና “ኤ ቡል ኢን ኤ ቻይና ሾፕ“ እንድሚሉት መሆን ነው። በጎው ነገር ለእውነት መቆም ነው። የእውነት ሐገሩ የነፍስ ሀቅ መገኛው ቅዱስ ህሊና ነው። ግንኙነታችሁ ምንም ይሁን ምን ንጽህ መስታዋት ሆናችሁ እድፉን ማሳየት ካልቻላችሁ እና ክእብደቱ መመለስ ካልቻላችሁት ምን ትጠቅሙታላችሁ? ብዙዎች በአድናቆት እና በጭብጨባ ጠፍተዋል። ነፍሳቸው ከንቱ ውዳሴን እንቢ ያለቻቸው ደግሞ ታሪካቸው ሁሉ ለብነ ሆኖ አልፏል። የህሊና ዝቅጠት የጥልቀቱ መጨረሻው እንጦርጦስ መሆኑን አቅም ካላችሁ ንገሩት። ናዚዎቹ ከአይሁዶቹ መሀል ጉልበት ያላቸውን እየመረጡ የገዛ ወገኖቻቸውን አስከሬን እንዲያቃጥሉላቸው ይጠቀሙባቸው ነበር። “ሶንደር ኮማንዶ” ይሏቸዋል። ግንኑኙነታቸው መርዛማ ስለነበር አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ በተራቸው ይገደሉና በሌላ ይተኳቸው እንደነበር ከታሪክ ድርሳናት ብቻ ሳይሆን ዛሬም ድረስ ከእልቂቱ የተረፉት ምስክሮች የሚሉት ሀቀ ነው። ከዚህ በላይ በሥጋም በነፍስም መክሰር የሚቻል አይመስለኝም።

አንተነህ ነኝ፣
ከለነደን፣